# አሲምባ ርዕሰ አንቀጽ

Editor's Note ቁጥር 1/2010


# ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም።

ጭቆና ባለበት ቦታ ሁሉ ሕዝባዊ አመጽና አልገዛም ባይነት አይቀሬ ነው። ዛሬ በሀገራችን እየተቀሰቀሰ ያለው ሕዝባዊ አመጽ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላለፉት 27 ዓመታት የወያኔን ዘረኞች የክልል ፖለቲካ የጭቆናን አገዛዝ በቃኝ ብሎ ሰንሰለቱን በጣጥሶ እንደ አንድ ሰው ሊነሳ እያኮበኮበ እንዳለ ግልጽ የሚያደርጉልን ምልክቶችን እያየን ያለንበት ታሪካዊ ወቅት ላይ ደርሰናል። በተለይም የሕዝቡን ድፍረትና ተጋፊነት ያስቸኳይ ጊዜውም አዋጅ ሳያበርደው እያደገ የመጣው የእምቢተኝነትና ከየአቅጣጫው በወያኔ ላይ እየከረረ የመጣው ጥላቻ በየዕለቱ እየጎመራ መምጣቱን እየታዘብን ነው። የሕዝቡ ቁጣና ስሜት ከመቼውም ጊዜ የጠነከረ ለመሆኑ በየካቲት 66ቱ ሕዝባዊ አመጽ ጊዜ የነበርን እንደምናስታውሰው፤ ሕዝብ አልገዛም ብሎ ሲነሳሳና ያለው ሥርዓት መግዛት በማይችልበት ወቅት በሀገሪቱ ይታይ የነበረውን ዓይነት የአብዮቱን አይቀሬ ፍንዳታ ጊዜ የነበረውን ስሜት ያስታውሰናል። ይህን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ደግሞ ማንም ሊገድበው፣ ሊያቆመው የማይችል ኃይለኛ ሕዝባዊ ማዕበልን ስለሚያስከትል የኃይል ሚዛን ወደ ሕዝብ ጎን የሚያጋድልበት፣ የገዢው ሥርዓት የሚርድበት፣ የሚፍረከረክበት ስለሚሆን የገዢው ክፍል ከዕለት ወደ ዕለት በኃይልና በጉልበት የያዘው ሥልጣን ከመዳፉ እያፈተለከ ከቁጥጥሩ ውጭ የሚወጣበት ጊዜ አጭር እየሆነ መጥቷል። የወያኔው የዘረኝነት ሥርዓት የሚተማመንባቸው የፋይናንስ፣ የቢሮክራሲ፣ የስለላ፣ የወታደራዊ ተቋሞች፤ የክልል የግዛት አስተዳደር ሰንሰለቶችም ሆነ የፕሮፓጋንዳ አውታሮች ወያኔ እንደሚፈልገው ሊታዘዙለት የማይችሉበት አጣብቂኝ ውስጥ መወርወሩ ደግሞ አይቀሬ ነው። ወያኔዎቹ በቅርቡ በመቀሌ ተሰብስበው በድርጅታቸው ውስጥ የሚታየውን መሰነጣጠቅ ጠግነው መውጣት አለመቻላቸውና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በየክልሉ ያሉ አስተዳደሮች ከወያኔ ልጓም ራሳቸውን ለማላቀቅ የሚያደርጉት መንፈራገጥ፣ (በቅርቡ እንኳን ቱባ የወያኔ በለሥልጣኖችና ተለጣፊዎቻቸው የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤ አቅርበናል ወሬም እያሰሙን ነው) ሁሉም የሚያመላክቱን የወያኔ የዕዝ ሰንሰለት በስብሶና በሽቅቆ እየረገበ የመጣበት ደረጃ መድረሱን ነው።

ቀደም ተብሎ ታውጆ የነበረው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የብዙ ወገኖችን ምስዋዕትነትና በየእሥር ቤቱ መጋዝን ቢያስከትልም የህዝቡን አመጽ ይበልጥ አጎለበተው እንጂ አላቀዘቀዘውም። በጥሞናም ለተመለከተ የወያኔ ሥርዓት የተርበተበትን ጊዜ አመላከተ እንጂ በቃኝ ብሎ የተነሳን ሕዝብ ክንድ እንኳን ሊያለዝበው አልቻለም። እንዲያውም የሕዝቡ ቁጣ ከረር፤ ጠበቅ እያለ ነው የሄደው። ወያኔ በምዕራባውያን እርዳታ አዲስ አበባ ገብቶ በሚኒሊክ ቤተመንግሥት በሥልጣን ኮርቻ ላይ ከተቀመጠ ጀምሮ ላለፉት 27 ዓመታት የሕዝቡን መነሳሳት በየጊዜው በኃይል ዝም አሰኝቶ እንዲወጣው የሚጸልዩለት ደጋፊዎቹ (አገር በቀልም ይሁኑ የውጪዎቹ) ሕዝቡ ኃይል ሚዛኑን ሲደፋ ሰልፋቸውን በቅጽበት እንደሚያስተካክሉ የታወቀ ነው። እንዲያውም በሚያስደንቅ ሁናቴ ወያኔን በማውገዝ በሥልጣን ላይ ያሉት ይሰቀሉ ጩኸታቸውን ማሰማታቸው አይቀሬ ለመሆኑ ከታሪክ በማጣቀስ ብዙ ማለት ይቻላል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ዓይነት ቀውጢና የሥር ነቀል ሕዝባዊ አመጽ ጊዜ በተደጋጋሚ ያለፈ ስለሆነ በዚያ ውስጥ ያለፍን ሆነ ላላወቅነውና ላላጤንን፣ ዛሬ ደግሞ ያለው ሥርዓት ደጋፊዎችና የሥርዓቱ ፕሮፓጋንዳ ክፍል ራሱን ለማዳን በሚያደርገው የመዓት ወሬ ወቅቱ ሊያሰፈራን፣ ሊያደናግረን ይችል ይሆናል። ግና ያህ ወቅት ፈራነውም ተደናገጥን ልክ እናት ከዘጠኝ ወራት እርግዝና በኋላ የወሊዱ ቀን ሲደርስ፣ አምጣና ተጨንቃ መውለዷ አይቀሬ መሆኑንና፤ በእርግጥ በወሊዱ ጊዜ ያልተጠበቁት ብዙ ሁናቴዎች በእናቲቱም ሆነ በሚወለደው ህጻን ሊደርሱ እንደሚችሉ ቤተ-ሰቦችና ወዳጆች ቢገምቱም፤ የሕፃኑን መወለድ በብሩህ ተስፋ ይጠብቁታል እንጂ በፍርሃት ተሸማቀው አይቀመጡም። ልጁም ሲወለድ በዕልልታ የሚቀበሉት እንጂ የሚደናገጡበት ወቅት አይሆንም። ይህም እየተነሳሳ ያለው ሕዝባዊ አመጽም ሊያመጣ የሚችለውን ለውጥ በግምትና በተስፋ በማሰብ ሀገር ወዳዶች ሁሉ ድጋፋችንን በያለንበት ልንሰጠውና ተዘጋጅተንም ልንጠብቀው ይገባል።እንደራጅ! እንደራጅ! እንደራጅና አምርረን እንታገል የምንለውም ለዚሁ ነው።

# አሲምባ ርዕስ አንቀጽ

Editor's Note ቁጥር 1/2010

ለውጥ የሚፈልገውና ሀገር ወዳዱ ክፍል ይህን ወቅት የሚፈራው ጊዜ ከቶውንም ሊሆን አይገባም። አዎን ወያኔዎችና ተለጣፊዎቻቸው ይህ ሕዝባዊ አመጽ ጠራርጎ የሚያጠፋቸው እንደሆነ ስለሚያውቁ ሕዝቡን ለመሸንገል አይቧጥጡት ዘዴ፣ አይፈነቅሉት ድንጋይ፣ የማይደረድሩት ውሸት የለም። ካልሆነላቸው ደግሞ ኃይልንም በመጠቀም ራሳቸውን ከሥልጣን ኮርቻው ላይ እንዳሉ ለማስቀጠል የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ። የሕዝቡንም ድምጽና ጩኸት እየጮኹ አቅጣጫ ለማሳት የሚቻላቸውን ሁሉ ማድረጋቸው አይቀሬ ነው። ሕዝቡ ወደ እርስ በእርስ ጦርነት ቢገባም ደንታ የላቸውም። በቅርቡ በየቦታ የምናያቸው በዘር ያተኮሩ መገዳደሎች፤ ለኳስ ጨዋታ የሚሰበሰብ ሕዝብ እንኳ በጨዋታው ተዝናንቶ ወደ ቤቱ ከመሄዱ ይልቅ በጥላቻ ግርግር በወገኖች የደረሱ ጉዳቶችና የንብረት ውድመቶች፤ በከፍተኛ የትምሕርት ተቋምት ሳይቀር በዘር ላይ ያተኮረ መገዳደል ከሚካሄዱባቸው ጀርባ በወያኔ የሠለጠኑ ልዩ ወታደራዊ ተቋማትና የስለላ ክፍሎች እጅ ለመኖራቸው አንጠራጠርም።

ይህ ሁሉ ለምን? ብለን ብንጠይቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን የሚታገልበት መንገድ በየክልሉ የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄ፣ የአማራው መብት፣ የጋምቤላው ሕዝብ መብት ረገጣ ... ወዘተ. እያለ ወያኔ በቆፈረለት የዘር ቦይ ውስጥ ብቻ መወሰኑ በወያኔ ተነጥሎ መመታት ያመቻቸው መሆኑን ተረድቶ ትግሉን ሕብረ-ብሔራዊ መልክ ለማስያዝ መጠቃቀስ መጀመሩ የወያኔና የዘረኝነት ፖለቲካ ግብዓተ-መቃብር መሆኑን ወያኔዎቹ ጠንቅቀው ስለሚረዱና ስለተደናገጡም ነው። ስለሆነም በኢትዮጵያውያን መካከል ያለው አለመተማመን እንዲቀጥል፤ ሀገር አቀፉ ትግል ጠንካራ ኃይል ሆኖ እንዳይወጣ የሚከፋፍለንን መርዝና ተንኮል በመካከላችን በመርጨት ሁሉም ሕመሙ አንድ ሆኖ ትግሉን ከማቀነባበር ይልቅ በጎሪጥ እንድንተያይ የተቻላቸውን ሁሉ እያደረጉ ነው።

ትኩረታችንም በወያኔ ላይ እንዳይሆን ሕብረተሰባችን እርስ በርሱ የሚነካከስበትንና የሚነታረክበትን የውሸት ፕሮፓጋንዳና አዳዲስ አጀንዳዎች በማስጨበጥ ሁናቴውን ለወያኔ ማመቻቸት ደግሞ ሌላው ጨዋታቸው ነው። ሰሞኑን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኢሕአፓ ላይ የሚዥጎደጎዱትን የፈጠራ የታሪክ ክለሳዎችን ለተመለከትን፤ ሕዝቡን አቅጣጫ ሊያሲዙ የሚችሉ እንደ ኢሕአፓ ያሉ ጠንካራ ሕብረ-ብሔራዊ ድርጅቶች ተሰሚነት እንዳይኖራቸው የሚያደርጉት ተንኮል ነው። ሕዝቡም እስኪነቃበቸው ድረስ ትግሉን ዕልህ አስጨራሽና ረዢም እንዲሆን አድርገውታል። በሌላ በኩል ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ ሀገር በቀል የወያኔ ደጋፊዎች ሥርዓቱ መንገዳገዱን ተመልክተው ከፎቅ እንደ ተወረወረ ሸክላ ብትንትኑ ሳይወጣ እንደ ኳስ ንጥሮ ሊድን የሚችልበትን ዓይነት ሁናቴን ለወያኔ ለማመቻቸት ሲራወጡ እያየን ነው። ወያኔን ጠግኖ በሌላ መልክ ለማስቀጠል የተለያዩ ማጃጃያ ተንኮሎችም እየተሸረቡ ነው። ወያኔን ያዋለደው የአሜሪካው ዴፕሎማት ሄርመን ኮኸን የሰሞኑን ሸር ጉድ መመልከቱ በቂ ምስክር ነው። የሀገሩን ሠርዶ በሀገሩ በሬ እንዲሉ የሀገራችን ችግር የሚፈታው እኛው በእኛ ብቻ መሆኑን ማስረገጥ የሁላችን ተግባር ነው። "በኢትዮጵያ ጉዳይ ፈረንጅን ምን አገባው?" እንዳለው የፍኖተ-ዴሞክራሲ ራዲዮ ጣቢያ ሀተታ ማለት ነው። ከላይ የተሰመረበትን ጨቆን በማድረግ ሙሉ ሀተታውን ማድመጥ ይቻላል።

በነገራችን ላይ ከተቃዋሚውም መካከል ራሳቸውን ሥልጣን ላይ ለማውጣት አጋጣሚ ያገኙ የሚመሥላቸው ማፈሪያዎችም በነ ሄርመን ኮኸን ዓይነት ቦይ መፍሰሳቸው የሚጠበቅ ነው። ሁሌም እንደምናየው የሕዝቡ ትግል ትንሽ አየል ሲል ትግሉን እንመራለን የሚሉን ድርጅቶች፣ መድረኮች፣ የዘር እምባ ጠባቂዎች፣ ገላጋይ የሀበር ሽማግሌዎች፣ ጠበብት አዋቂዎች ወዘተ. ሕዝቡ ያልመረጣቸው ባተሌዎች፤ የሽግግር መንግሥት መሥራቾች ነን ባዮች ባጠቃላይ የድል አጥቢያ አርበኞችም ከየጎሬአቸው ኮተታቸውን በዘምቢል ሞልተው ብቅ ቢሉም ወጣም ወረደ ለሀገራችን መፍትሄው ሁሉን ያካተተ ምክክር ማድረግ ብቻ መሆኑን ልናመላክታቸው ይገባል። እንግዲህ ወያኔን በሌላ መልክ ለማስቀጠል የሚደረገውን አሻጥር ሁሉ በንቃት በመከታተል የማጋለጡ የሀገር ወዳዱ ሥራ ነው። የሀገራችን ሰው ከላይ እንደተዘረዘረው ወያኔን በተሃድሶ ጠበል የማጥመቅ ሸርጉድ ዓይነቱን "ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም" ይለዋልና እኛም እንዲሁ የወያኔን ሥርዓት ከነሰንኮፉ (ተለጣፉዎቹን ጨምሮ) ማፈራረስ እንጂ መለጣጠፍ የፍትሕ ሥርዓትን ሊያመጣ እንደማይችል ተገንዝበን በተቀነባበረ መልክ ትግሉን እንቀላቀል፤ እናጧጡፍ።

# አሲምባ ርዕስ አንቀጽ

Editor’s Note ቁጥር 1/2010

ለማጠቃለል፥

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጭቆናን አስወግዶ የሥልጣኑ ባለቤት ሊሆን የሚችልበት ዛሬ የተደረሰበት ዓይነት የለውጥ መስቀልኛ መንገድ ላይ ከአንድም ሁለት ጊዜ ደርሶ (የዓፄውና የደርግ መንግሥት ሲወድቁ ማለት ነው) የትግሉን ፍሬ ብልጣብልጥ የሥልጣን ጩሉሌዎችና በምዕራባውያን ጉልበት ተረድተው የመጡ ወያኔዎች ነጥቀው በተራቸው እስኪወድቁ ሕዝቡን ቀጥቅጠው ሊገዙ ችለዋል። ያም የሆነበት ዋና ምክንያት ሕዝቡ የኔ በሚለው ጠንካራ ሕዝባዊ ድርጅቶች ተሰባስቦ ባለመገኘቱ ነው። በአፄው ጊዜ በአንፃሩ ተጠናክሮ የተደራጀው ኃይል ወታደሩ ብቻ ስለነበር፣ ከዚያው የተውጣጣው የምርጥ መኮንኖች ቢድን አባላት ለሥልጣን ሲሉ ጠንካራ ድርጅቶች እንዳይወጡ ትውልድ መትረው ሀገር አጥፍተው በምዕራባውያን እርዳታ ሀገር የሚጠሉ ወያኔዎችና ሻቢያዎች ሥልጣን ላይ እንዲወጡ አስችለዋቸዋል። ካለፉ ሁለት የለውጥ ወቅቶች እንደምንማረው ኢትዮጵያውያን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ትግላችንን <u>በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ብቻ በማቀነባበር</u> ሁላችንም ወደ አንድ አቅጣጫ የምንገፋ የማንበገር ኃይል ሆነን መውጣት ይጠበቅብናል። ወያኔዎች ይህ ኢትዮጵያዊ ኃይል ተቀነባብሮ እንደ አንድ ሰው እንዳይወጣ ማድረጋቸው አይቀሬ ነው። እያደረጉም ነው። ዛሬ ለኢትዮጵያ እንታገላለን የሚሉን ብዙ ድርጅቶች በፖለቲካው መድረክ ሲሽከረከሩ ቢታዩም ማናቸውም ጠንክረው መውጣት ስላልቻሉና፤ በወያኔም ተነጥሎ ለመመታት የተመቻቹ ስለሆነ እነሆ ወያኔ ሕዝቡ እየጠላው፣ በራሱም እንኳን የደከመ ቢሆንም ሥልጣን ላይ መቆየት በቅቷል። ዛሬ ወያኔ ሀገራችንን በዘር ክልል አጥሮ አንዱ ከሌላው እንዳይነጋገር ተብትቦ በያዘበት ወቅት በስብሶ በራሱ ክብደት እንኳን ቢወድቅ በየቦታው በተቀበረው የዘርና የኃይማኖት ፈንጂዎች ወገኖች እርስ በእርስ እንዳይጨራረሱ ሀገር ወዳዶች ሕብረ-ብሔራዊ ስሜትን በማጠንከር በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ትግሉ ሊቀነባበር የሚችልበትን ሁናቴ በአጭር ጊዜ ውስጥ ማመቻቸት ወይም ማቀነባበር ይጠበቅባቸዋል። የኢትዮጵያ ሀገራችን ችግር የሚፈታው በኢትዮጵያውያንና በሚያደራጁቸው ድርጅቶች ብቻ ነው። ስለሆነም በየድርጅቶች ውስጥ ያለን ሀገር ወዳዶች ድርጅታችን ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ጋር ትግሎቻቸውን እንዲያቀነባብሩ ከፍተኛ ግፊት ማድረግ ይጠበቅብናል። ሁላችንም ልንገነዘበው የሚገባው ሕዝቡ የሥልጣኑ ባለቤት እስካልሆነ ድረስ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሀገራችን ለመገንባት አለመቻሉን ነው።

ድር ቢያብር አንበሳ ያሥር እንዲሉ ኢትዮጵያውያን በመካከላችን መተማመንን በጥንቃቄ እንገንባ!

ለአንዴም ለመጨረሻ ጊዜ የሕግ የበላይነት በኢትዩጵያ ዕውን እንዲሆን ትግላችንን አስተባብረን ትግሉን እናፋፍም!

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላች ያቸንፋል!

የአሲምባ ድረ-ገጽ ዝግጅት ክፍል